ለዶ/ር አብይ አህመድ  ሰላም ይሁንለዎ! መልካም የስራ ዘመን ለእርሰዎና ለሚወዶት ኢትዮጵያ!

ለሃገራችን እውን ለውጥ እንጠብቅ አሁን ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት  ምንድን ነው?

የኢትዮጵያ ሕዝብ መሰረታዊ ችግሮች ምንድን ናቸው የመለውን ለይቶ ለማወቅ ከሕዝብ ጋር መወያየት ቢሞክሩ?

አዲሱ ካብኔ እነማን ይሆኑ? ሚኒስተር ለመሆን መሰፈርቱ ምንድን ነው? እና አዲሱ ካብኔ የማይሰርቅ፣የማይዘረፍ፣የማይገድል፣የማያሳፍን፣የጎጠኝት በሽታ ያልያዘው/ያልያዛት፣ሃገራቸውን፣ወገናቸውን የማይጎዱ/የማይክዱ/፣ችግር እያለ ችግር የለም የማይሉ መሃይም ምሁራን ያልሆኑ፣በሽፍጥ ያልተሞሉ፣ቅን አሳቢዎች ሰው ሰው የሚሸቱ ከጎሳ ነጻ አስተሳሰብ ሙሉበሙሉ ነጻ የሆኑ ፣ ሃገርን የማይሸጡ፣ከጠላት ጋር አብረው የሃገርን ጥቅም አሳልፈው የማይሰጡና ለኢትዮጵያ አንድነት ዘብ ብቻ ሳይሆን ሕይወታቸውን አሳልፈው የሚሰጡ እስከ አሁን ድረስ ከወያኔ ጋር አብረው የሃገርን ሃብት ያልዘረፉና ያልሰረቁ ሃብት ያላካበቱ ቢሆን መልካም ነው ውጤት እናመጣን እኔም ከጎናችሁ ነኝ ያለጥርጥር አረጋግጥለሁ፡፡

ህዝብን በሃማኖትና በጎሳ ሳይከፋፍሉ ሌት ተቀን የሚጥሩ ምሁራን፣ቅን አሳቢ ሰዎችን ማወያየት ዋና ስራዎ መሆን አለባቸው /አለበት

## የሃብት ክፍፍል

ይህ ሃብት የሚባል በሃገራችን ክፋትን ተንኮልን ከዘራብን ሰንቶል ይባስ ብሎ አሁን እየገደሉ፣እየዘረፉ ሃገርን ወደብ አልባ ያደረጉ ሃይሎች ሃገሪቱ እነሱና የእነሱ ብቻ ናት! አትንኩብን እየገደልንና እያፈንን የመጣነው 60 ሺህ ሰዎች ያስጨረስነው ለሃብት መሆኑ ይታወቅልን ያለው ምሳሌ ለምጥቀስ

1-ገብረወሃድ የኩምርኩ ምክትል ስራ አስኪያጂ ያለው ሃብት መጠን 1- 27 ቤት ከነካርታው፣2- 54 መኪናዎች፣3- አንድ ሚሊዮን ዮሮ በቢሮ ውስጥ የተገኝ፣4- 500 000 ዶላር፣5- የኢትዮጵያ ብር መጠን ለመቁጠር አስቸጋሪ እንደነበር በወቅቱ በፍተሻው የተገኝ የአይን እማኞች ነግረውናል(ምንጭ፡ የኢዜአ/

2- ሌላው ወያኔ በህገመንግስቱ መሬት መሸጥ መለወጥ አይቻልም ይለናል ግን ልብ በሉ እነሱ በካሬሜትር 365000(ሶስትመቶ ስልሳ  አምስት ሺህ ብር) ይሸጣሉ

3- በመስሪያ ቤቶች ውስጥ ያሉ ወያኔና የወያኔ ተላላኪ ካድሬዎች ያላቸው ሃብት መጠን በጣም ብዙና ከፍተኛ ነው ምሳሌ አንድ ካድሬ ከአምስት ቤት በላይ ያለቸው ሲሆኑ እነሱ ግን ቤታቸውን አከራይተው በህዝብ ቤት ማለት ወያኔ በሰጣቸው ኪራይ ቤቶች ውስጥ ይኖራሉ ይባስ ብሎ እዚያው ኪራይ ቤት አከራይተው የሃገሪቱን ዜጎች በማሰር፣በመግደል፣በማፈን ስራ ላይ ተሰማርተዋል በመስሪያ ቤት ውስጥ ያለውን ዘርፋ፣ቅሚያ፣ነጠቃ፣አይን ያወጣ ጉቦ ሰብሳቢዎች ናቸው፡፡

## ትምህርትን በተመለከተ

ዛሬ በሃገራችን ትምህርት አለ ማለት ራስን ማታለል፣ማጭበርበር ሃገርን መክዳት ነው፡፡ሳይማሩ የሚመረቁባት፣ይባስ ብሎ በማዕረግ የሚያሰመርቁባት (ምሳሌ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ንግድ ስራ ኮሌጅ ከፍተኛ ማዕረግ ማስመረቅ በወቅቱ የትምህርት ሚ/ር የነበሩት ወ/ሮ ገነት ዘውደ ለሃገሪቱ ፓርላማ ማቅረባቸውን ማስታወስ እዚች ሃገር ምን እየተሰራ ነው) በትምህርት ቤቶች ዙሪያ የሚሸጠው (ሽሻ፣ጫት፣ጠላ፣ሲጋራ፣ሃሽሽ፣ሴተኛ አዳሪዎቸን አሰልፈው) ተማሪዎችን እያስተማርን ነው የሚሉ የእነሰብሃት ነጋ ቡድን የተማረ መሃይም ለማፍራት ተግተው እየሰሩ መሆናቸውን በተግባር ላይ አውለውታል በሃገሪቱ የተከፈቱ ዩኒቨርሲቲዎች ብዛት ቢጨምርም ተመርቆ የሚወጣው ተማሪ የተማሩ አለመሆናቸው ከራሳቸው ከተመራቂዎች አንደበት እውን ነው በትክክል ነግረውናል የሚያስተምሩት መምህራን ለማስተማር አይደለም ለመማር ብቁ አይደሉም በሰላሎች፣በአፋኛች የተከበበ ከፍተኛ ተቆም ብዙዎቹ የሃሰት(ፎሪግድ) የትምህርት ማስረጃ ያላቸው መሆናውን በሃገሪቱ ዜና ማሰራጫ አንድንዶቹም ያመኑት ጉዳይ ነው

በመስሪያ ቤቶች የሚቀተሩት የአንድ ጎሳ ብቻ ያለውም ትግረኛ ተናጋሪ መሆናቸው እኛ ብቻ ነን መኖር ያለብን ተባብረው ሌላውን ከስራ ያፈናቅላሉ/እያፈናቀሉን ነው

1- ለምሳሌ በጋምቤላ መስተዳደር ውስጥ 220 የሀሰት ማሰረጃ መገኙቱ ማሳያ ነው ይህ ለምን እና በማን ተደረገ ማስረጃውን ያዘጋጀው ወያኔ አይደለምን

2- በአሶሳ ዮኒቨርሲቲ 120 መምህራን መገኘታቸው

3- በአማራ ክልል ራሳቸው በማጋለጥ አጭበርባሪዎቹ 1550 በላይ የተሳሳተ የትምህርት ማስረጃ አቅረበዋል

4-በኦሮሚዊ ክልላዊ መንግስት ከ6500 በላይ

- 5- በአዲስ አበባ መስተዳደር 1000 በላይ ይህ መረጃ የተገኘው ከሃገሪቱ ቴሌቭዥን መሆኑ እውቁልኝ በሱማሌ፣በደቡብ፣በአፋሪ፣ሆድ ይፍጀው እነዚህ ናቸው ጅቲፐ 1 እና ጅቲፐ2 አዘጋጅተው እድገት አለ የሚሉን እሚያሳዝነው አንዱም በስራ ላይ አልዋለም ምክንያቱም ኢትዮጵያ ብሔራዊ እቅድ አላዘጋጀችም በደንቆሮ እንደት ብሎ **በወያኔ ዘመን ተማሪዎች ትምህርት ቤት ገቡ ሌብነትን ተምረው ወጡ**?

  **(አማራ መንገድ ላይ ሲለምን ማየት እፈልጋለሁ /መለስ ዜናዊ/**

6- በኢትዮጵያ ስርዓት ትምህርት ጉዳይ ምን ምንጊዜም በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የማትተኛው እንግሊዝ ከጥንት ጀምሮ የጥፋት ክንዶን አሁንም በርዳታ ሰበብ የሃሰት መረጃ ከሚሰጡት የምዕራባዊያን መንግስታ አንዱ ቢሊዩን ፓውንድ

(1 000 000 000 ፓውንድ)/ ምንጭ:የጀርመን ሬድዮ 20101 ዓ.ም)

ለባለስጣናት ትምህርት በማለት ዛሬ ሚኒስቴር፣ደታ፣ኢኮኖሚስት አዲስ አበባ ሎንደን እየተመላለሱ ተማርን ድግሪ ይዘናል ይሰጣሉ ምን ታመጣላችሁ/ አሜሪካም ሆነች እንግሊዝ ከኢትዮጵያ አጥፊዎችና ነቀረሳዎች መሆናቸው በአደባባይ ነግረውናል

## <u>በሃገሪቱ ያሉ ፕሮጀክቶች</u>

ፕሮጀክት ገደብ ነበረው ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ፕሮጀክት የሚነደፈው ለኪስ ማደለቢያ/ለነጣቂዎችና አስነጣቂዎች)፣የሃገርና የሕዝብ ጠላት ለሆኑ ጅቦች፣ ገንዘብ መሰብሰቢያ፣ብዙ ቤቶችን ለባለስልጣናት ለመስራት የፕሮጀክት አስተባባሪዎች ተብየዎች ሲሰርቁ፣ሲዘርፉ፣ሲያጠፋ አንድም ፕሮጀክት እውን አልሆነም ( ስለዚህ ፕሮጀክቶች የሚነደፉት በጠላቶቻችን እቅድ እጅ ነው ማለት ነው) ለጠላቶች መጥፊዋ የሚነደፍላት ሃገር መሆን የለባትም (ምሳሌ: መንገዶች ግድቦች፣የቤቶች፣40/60፣20/80፣ወዘተ

## <u>የተገደሉ ኢትዮጵያዊያን</u>

ሰውን መግደል በኢትዮጵያ ዋና ስራ ነው ይህም ቀደም ብሎ በ1981ዓ.ም በአሶሳ 6000 (ስድስት ሽህ) አማራዎች፣በ1983 በሃርር፣በአሩሲ፣በባሌ፣በሲደሞ፣በወለጋ፣ በጎንደር ወልቃይት፣በጋምቤላ፣በኦጋደን) ወዘተ ሰንት ናቸው?

በ2010 ዓ.ም በሃገራቸው የተገደሉ፣ከሃገራቸው የተባረሩ አንደ ሚሊዮን የኦሮሞ ሕዝቦች ዛሬ ኢትዮጵያ በወራሪዎች ተወራለች በወያኔ፣በብአዲን በስንቱ!

በመላው ሃገሪቱ ሰውን የገደሉ፣ያቆሰሉ፣የዘረፉ፣ደብዛውን ያጠፉ፣ጥፍርን የነቀሉ፣ የደፈሩ፣እርቀነ ስጋቸውን ልብስ አስወልቀው የገረፉ፣መግረፊያው ያቀረቡ ለምሳሌ እንደነ ዶ/ር አሽብር ወልደጊውርጊስ ይህ ሰው የፓሊስን ዱላ ገዝቶ በማቅረብ ይታወቃል ሕዝብ ይህን ሊያውቅ ይገባዋል፣ጥርስን ያስነቀሉ፣አይን ያስጠፉ ፣ ትዕዛዞችን የሰጡ የተቀበሉ፣ጫካ ውስጥ ገድለው ለጅብ የሰጡ ሁሉ (ሚኒስቶሮች፣ ካቢኔዎች፣ሕዝብ ተወካዮች ፣ካድሬዎች፣የወረዳ አስተዳዳሪዎች፣የቀለቤ ተመራጮች በሃገሪቱ ለተፈጸመው ግፍና በደል ተጠያቂ መሆን አለባቸው ለፍርድ እንድቀርቡ ሕዝብ በትብብር በሃገሪቱ ሕግና በአለምአቀፍ ሕግ በመታገዝ ፍትህ ማገኝት አለብን ደብዛቸው የጠፉትን ሰዎች ሁሉ የቀበሩበትን ቦታ ገዳዮዎቹ ለቤተሰቦቻቸውና ለህግ ክፍል ማሳወቅና መጠቆም አለባቸው

## <u>በሱማሌ ክልል የተዘጋጀው ልዩ ሃይል</u>

መጀመሪያ ለምን ልዩ ሃይል ለምን አስፈለገ? ይህ እቅድ የተነደፈው በሎንደን ውስጥ ሲሆን ያም የሆነው እንግሊዝ የልዩ ሃይሎቹን ማሰልጠኛ ገንዘብ ባጀት ለመመደብና ኦሮሞውንና አማው በሃገሩ ለማስገደል፣ለማባረር ለዚህም እንግሊዝ አስራአምስት ሚሊዩን ፓውንድ (15 000 000 ፓውንድ)(ምንጭ፣የድላ ዩኒቨርሲት መምህራን በአሜሪካን ሬድዮ የተነገር) በመመደብና አሰልጣኝ አስተማሪዎችን በመመደብ ምን ጊዜም በትውልድ የሚፈለዳ ፈንጅ አጥምደው ያሁም ትውልድ ቀምሶ ከሃገሩ አይግባኝ ጠፋ ሆድይፍጀው

## <u>የርዳታ ሰችዎች ስውር ደባ</u>

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚተረማመሰው የረዳታ ሰጭ ብዛት የሚያውቁት እነሱና በርዳታ ሰጭዎች ድርጅቶች የሚሰሩ የሃገሪቱና የውጭ ሃገር ተወላጆች በገንዘብ፣ በመኪና፣በውጭ ጉዞ ገንዘብ መሰብሰብ በሆቴች መዝናናት ሆዳቸውን መሙላት፣ የሃገርን ሃብት ከርዳታ ሰጭዎች ጋር ተባብረው እጽዋትን፣እንስሳትን፣ሰብሎችን

፣ሰዎችን በኮንትሮባንድ፣በይፋ፣በድብቅ ከሃገር ማስወጣትና ከፍተኛ ሃብት የሚያካብቱት በድሃ ሕዝብ ስም በየትኛው ህግ ይዳኛሉ ?

## የመሬት ቅርምት ዘመን

በ21ኛው ክፍለ ዘመን ታይቶም ተሰምቶም እማይታወቅ በኢትዮጵያዊያ ላይ የተሰራ ግፍና በደል ምንጊዜም አይረሳም! ገበሬውን ከማሳው ላይ አፈናቅለው፣ ገድለው፣እስረ ቤት ከተው፣ካሳውን ነጥቀው፣መሬቱን የእስር ቤት ገንብተው፣ስደት እንደሂድ ከነቤተሰቡ በጥቅሉ የዘር ማጥፋት ወንጀል ነው።።በተግባር ሰረተዋል

ስንደ፣ማኛ ጤፍ የእልህ አይነቶችን የሚመረትበትን የኢትዮጵያን መሬት ለአበባ እርሻ፣ለመርገዝ ማብቀያ አደረጉት የአፈር ጥራት ብክለትና የውሃ ብክለት ስንቱ ይዘርዘር ሌላ አንድ ምሳሌ እናንሳ ለመንገድ የመሬት ካሳ ክፍያ ለወሎ ገበሬ በካሬሜትር 25 ብር እስከ 300 ብር ያውም ከዚሁ ገንዘብ ላይ ካድሬው፣የወያኔ ቅጥረኛው ብአዲን፣ሲቀመንበሩ፣ተላላኪው ቀምተው ለርሃብና ለስደት ዳረጉት የጋንቤላን መሬት ለሳውድ አረቢያ፣ ለህንዶች፣ለፓኪስታኖች፣ለቱርኮች (ለሃገር ውስጥ ጅቦች ለወያኔ ቡድን ማለት ነው የሃገር ውስጥ  ጅቦች ለሰፈር ተጠራረተው የጋንቤላን ሕዝብ አፈናቅለውታል ገድለውታል። ሁለተኛ ምሳሌ አንደ ቤቱ ለባለሃብት(ባለሃብት ማለት ቀማኛው ነጣቂው ወያኔናተባባሪዎቹ ማለት ነው) ለመሸጥ የተፈለገ ቤት በደሴ ከተማ ውስጥ ነገሩ የሆነው ለአፈናቀሉት ሰው ቦታ ለባለሃብት ይፈለጋልና ካሳህን ይዘ ጥፋ ካሳው ስንት መሰላችሁ አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር (120 000 ብር) በግድ አባረው እነሱ ያን ቦታ ስድስት ሚሊዩን ብር (6 000 000 ብር) ሸጡት ይህን ነው የነቀርሳዎች ውጤት አማራውን መግደል፣ማፈናቀል፣ማፍን፣ማሳፍን ((**አማራ መንገድ ላይ ሲለምን ማየት እፈልጋለሁ /መለስ ዜናዊ/**

## ከሃገርና ከውጭ የወደሃገር ውስጥ የሚገቡ ምግቦች፣ሰብሎች፣መጠጦች ጉዳይ

ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ፈተና ውስጥ ከገባን ከ27 አመታት ሆነን ብዙ የሚያሳስበኝ የሚያስጨንቀኝ ከባድ ችግር ውስጥ ነው ያለች ሃገራችን በጎሳ በተደራጁ በአነስተኛና ቅጣጥን በቀለቤ በወረዳ ተደራጅተው ለህዝብ በሚቀርብ ሸቀጦች መድሃኒት ያልሆኑ መድሃኒቶችን በሌላ አነጋገር መርዝ ለህዝብ ማቅረብ ሲሆን

ኢትዮጵያዊያን የዘር ማጥፋት ዘመቻ መሆኑን መታወቅ አለበት በምግብ ውስጥ ባዕድ ምግቦች ከእንጀራ ውስጥ በመጨመር፣ጀሶ፣የግርግዳ ቀለም አፈር፣አሸዋ፣ቅቤ ውስጥ ድንች፣ሙዝ በመጨመር ዘይቱን በመርዝ በመለወስ ለህዝብ ቀርቦል ዜጎች ሞተዋል በሰው ተገድለዋል ማለት ነው ገዳዮም አቅራቢውም ወያኔና ወያኔዎች ናቸው አሁንም እያቀረቡ ናቸው ወያኔ ለምን የኢትዮጵያ ጠላቶች ሆኑ?

**የመፍትሔ ሃሳብ**

- የሃገሪቱን ስርዐት ትምህርት ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ እንድሸት በሃገር በቀል እውቀት ላይ መሰረት ያደረገ ሴክተር ሪቭው/የትምህርት አጠቃላይ  እና ጥናትና ጥራትን የጠበቀ እንዱሆን ማድረግ
- በመዋሸት ሃገርን መንግስትን አይጠቅም ይጎዳል እንጂ ከሁሉ ግን ማስመሰል አደጋ ነው
- ከህዝብ የተሰረቁ መሬቶች፣ንብረቶች፣ወርቆች፣ያልታወቁ ማዕድኖች ፣ ቤቶቻው፣መኪኖቻቸውን ለህዝብ ሳይውል ሳያድር መመለስ አለበት
- ከሕዝብ፣ከሃገር የተሰረቀ ማንኛውንም ሃብት ለሃገሪቱ ዜጎች ከድህነት መውጫ እንድሆን ማስመለስ ስራ ላይ ማወዋል
- ኢትዮጵያ ዛሬ የሚያስፈልጋት በእውቀት፣በትብብር የሚሰሩ ምሁራን እንጂ የሚሰርቁ ምሁራን ተብየዎች አትፈልግም
- በሆዳቸው የሚያስቡ ምሁራን ፈጽሞ ከሃገር መጥፋት አለባቸው!
- ህዝብን በሃማኖትና በጎሳ ሳይከፋፍሉ ሌት ተቀን የሚጥሩ ምሁራን፣ቅን አሳቢ ሰዎችን ማወያየት ዋና ስራዎ መሆን አለባቸው /አለበት
- ሃገራችን በአሁኑ ጊዜ በጣም የሚያስፈልጋት ዋና ነገር ቢኖር ዲስፒሊን/ስነ-ስርኣት/ ያለው/ያላት  ነው
- ሕዝብን አብሮ እንድኖር የሚሰብኩ

- ከሌብነት፣ከስርቆት፣ከዘረኝነት፣ከጎጠኝነት ነጻ የሆኑ ምሁራን ማብዛት
- እስከአሁን ድረስ ከህዝብ ከሃገራቸው ገንዘብ ያልሰረቁ ሰው ያልገደሉ፣ ያላስገደሉ በወገናቸው ላይ ግፍ ያልሰሩ
- በሃገሪቱ ባሉዩኒቨርሲቲዎች የሚማሩትን ተማሪዎች ኢትዮጵያዊነትን እንጂ መንደረተኝነት የማያስተምሩ ምርጥ ምርጥ ምሁራን በጥንቃቄ ማዘጋጀት እና ኢትዮጵያዊ የሆኑ ዜጎችን ኮትኩቶ ማፍራት
- «ትምህርት ቤቶች የነገውን ትውልድ የምናሳድግበት ክቡር ስፍራ ነው»!
- ስርዓት የሚለወጠው በስርዓት ነው! በትክክለኛ ሰው ብቻ!
- ህገመንግስቱን መሰረዝ፣አዲስ ሁሉም ያመነበትን በጥንቃቄ ማዘጋጀት
- በዘርፍ በዘርፍ ሙያቶኛችን ለሃገራቸው የሚያስቡትን ማዘጋጃት ነገር ግን ገንዘብን የሚያመልኩት ካንሰር እንዳይሆኑ መጠንቀቅ የወያኔ ሰለባ አለመሆን
- የተቀጠረ ግን የማይሰራ ሰው/ትውልድ/የማፍራት ዘመቻ ስለዚህ ትውልዱ ራሱንም ሆነ ሃገሩ ሊጠቅም አይችልም ይታሰብበት
- በሃገሪቱ ትክክለኛ ፓሊሲ እንድኖር መትጋት አዱሱ ጠቅላይ ሚ/ር ለዶ/ር አብይ አህመድ ብቻ የሚተው አይደለም

ሳ.አ